የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

ትዴት በወልቃይት ጸገዴና በራያ የማንነት ጥያቄ ላይ በሚነሱት ያለው አቋም

ባለፉት ሁለት ቀን ኢንጅነር ግደይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ባደረጉት ቃለመጠይቅ እና በጋዜጠኛው የተሳሳተ አቀራረብ የተነሳ በኢንጅነር ግደይ አቋምና በትዴት አቋም ጥያቄ ስላስነሳ ተገቢውን መልስ ለመስጠት ተገደናል። ጋዜጠኛዋ የጠቅላላውን ቃለመጠይቅ መንፈስ በማይገልጽና ያላልኩትን 'የራያ ህዝብ የማንነት ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኝ ት.ዲ.ት.ፓ ጠየቀ' የሚል አርእስት በመስጠት በመጀምሪያ ገጽ ማውጣቷ እንዲሁም በገጽ፲ ላይ 'በተለይ የራያ ህዝብ ጥያቄ ህግመንግስቱን መሰረት በማድረግ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት አለኝ' የሚለው ዘገባ የኔ ቃል ባለመሆኑ በጣም አዝኛለሁ፣ ለጋዜጣው አዘጋጅም ተቃውሞ አቅርቤ አለሁ። የቃለ ምልልሱ መንፈስና ይዘት በዝርዝር በዚሁ እትም በፖለትካ አምዱ ገጽ ፲፩ ላይ ማንበብ ይቻላል።

በወልቃይትና ጸገዴ ጉዳይ ቀደም ብለን የሰጠነው መግለጫ መኖሩን እያስታወስን አሁንም በተለያየ መልክ ህዝቡን ሊያወናብዱ ከሚፈልጉት አካላት ውሸጉበር እንዳይፈጠር በድጋሜ እንገልጻለን፣

ህዝቦች የማንነት ጥያቄን በማንኛውም ጊዜ የማንሳት መብታቸው ነው። ከዚሁም ተያይዞ ጥያቄውን የሚያቀርቡበት መንገድና ስርዓት በህገደንቡ የተቀመጠ ነው። በፈደራል ምክር ቤት አፈጉባኤ እንደተገለጸው በህገደንቡ መሰረት የቀረበ ጥያቄ እንደሌለ ግልጽ ሆኗል። ይህም ሆኖ ግን በአማራና በትግራይ ያለው ውጥረት በየቀኑ እየጨመረ በመሄዱ፣ በአማራ ክልል የትግራይ ተወላጆች በአማራ ሲጠቁ ሲገደሉና ሲባረሩ እንዲሁም ከአማራ ወደ ትግራይ የሚገቡት መንገዶች በመዘጋታቸው የትግራይ ህዝብ ተጠቂ በመሆኑ፣ የተጎዳው ህዝብ ካሳ እንዲያገኝ፣ መንገዱ እንዲከፈት፣ በትግራይ ላይ የሚደረገው ዛቻ እንዲቆምና በአማራ ክልል የትግራዎችን ጸጥታ እንዲጠበቅ የትግራይ ክልል መንግስት ጉዳዩን በቀጥታ ለፈደራል ምክር ቤት አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት ይገባል እንላለን። ይህ ጥቃትና ብጥብጥ ሲደረግ ቁጥጥር ያላደረጉት እንዲሁም ተባባሪ የሆኑት የአማራ ክልል መሪዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ ይገባል። የአማራ ክልል መንግስት በጥላቻ የተመሰረተ ጽንፍ ሃሳብ በመያዝ ህዝቡን እየነዳ በስልጣን ላይ ለመቆየትና ከተጠያቂነት ለማምለጥ መሆኑን ግልጽ እየሆነ መጥቷል። የትግራይ መንግስት እስካሁን ጉዳዩን ለፈደራል ምክር ቤት አለማቅረቡ ህዝቡን በፍራቻ እያሳበበ ለመጠቀም መሆኑ ይታየናል። የሁለቱም ክልል መሪዎች በህዝቡ ላይ ቁማር እየተጫወቱ መሆናቸውን ለሁሉም ግልጽ መሆን አለበት። በተነሱት ውዝግቦች ጥቃት እየደረሰበት ያለው የትግራይ ህዝብ ስለሆነ የትግራይ ክልል መንግስት ጉዳዩን ለፈደራል ምክር ቤት አቅርቦ በአፋጣኝ ውሳኔ ማግኘት አለበት እንላለን። ሂደቱና የምክር ቤቱ ውሳኔም ለህዝብ ግልጽ መሆን አለበት እንላለን።

የማንነት ጥያቄ በሚመለከት ህዝብን ወክሎ ትዴትም ይሁን ማንኛውም ድርጅት ወይም መንግስት ሊወስን አይችልም። ማንነቱ የሚወስነው ህዝቡ ራሱ ነው። አማራ ነኝ ለማለትም ትግራዋይ ነኝ ለማለትም ጥያቄውን የሚያነሳውም የሚወስነውም ህዝቡ ነው። ለዚሁም በህገደንቡ የተቀመጠ አሰራር አለ። በትዴት በኩል በታሪክ የነበረውን ድንበር በማንሳት ብዙ ጊዜ ማጥፋት አለብን ብሎ አያምንም። የክልል አቀራረጹ አዲስ ነው፣ ቋንቋን መሰረት ያደረገ ነው። አማራ የሚባል ክልል አልነበረም፣ ከትግራይም በዓፋርና በአገው መሬት ተወስዶበታል። ይህ ሁሉ አዲስ ነው። ስለዚህ ነበረ በሚለው ላይ ባናተኩር ይሻላል። አሁን ባለው ህገደንብ ክልሉ በትክክል አልተደረገም የሚል አካል ካለ ህገመንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት መሄድ ይጠበቅበታል። ጭራሹንም የአከላለል ህገደንቡን እንቃወማለን የሚል አካል ካለም ህግደንቡን ለመቀየር ህጋዊ በሆነ መንገድ በፓርላማና በፈደራል ምክርቤቱ ተቀባይነት አግኝቶ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚቀየርበት ሂደት መከተል አለበት እንላለን። ይህን ስንል ግን አሁን የተጀምረው ዲሞክራሲያዊ ሂደት በዚህ መንገድ ለመሄድ የሚፈቅድ ሆኖ መገኘት አለበት ከሚል እምነት ጭምር መሆኑንም ልናሰምርበት እንፈልጋለን።

ህዝብን በማደናበር አገር አይገነባም!!

ኢንጅነር ግደይ ዘርአጽዮን

ጥቅምት 24, 2011